የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2014 በጀት ዓመት መነሻ ዕቅድ

ህዳር 2014 ዓ.ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

## ማውጫ


መግቢያ ..... 3

ክፍል አንድ ..... 1

1. የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎች ..... 1

1.1. የሰው ሃብትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2013 ዓ.ም አፈፃፀም ግምገማ እንደ መነሻ ..... 1

1.1.1. አቅም ግንባታ ..... 1

1.1.2. ክትትልና ቁጥጥር ..... 1

1.1.3. ህግ አወጣጥ ..... 1

1.1.4. የመስክ ምልከታ ሥራዎች ..... 2

1.2. የውጫዊ ሁኔታዎች ግምገማ እንደ መነሻ ..... 2

1.2.1. ዕድሎች ..... 2

1.2.2. ስጋቶች ..... 2

ቁልፍ ችግር ..... 3

ቁልፍ ተግባር ..... 3

ክፍል ሁለት ..... 4

2. የ2014 ዓ.ም የቋሚ ኮሚቴው ዕቅድ ..... 4

2.1. የዕቅዱ አጠቃላይ ዓላማ ..... 4

2.2. የዕቅዱ ዝርዝር ዓላማዎች ..... 4

2.3. ለሰው ሃብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ዝርዝር ..... 5

2.4. የዝግጅት ምዕራፍ ሥራዎች ..... 5

2.5. የተግባር ምዕራፍ ሥራዎች ..... 6

2.6. ሙያዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ ..... 13

2.7. የማጠቃለያ ምዕራፍ ሥራዎች ..... 15

2.8. አጠቃላይ የዕቅዱ አፈፃፀም አቅጣጫዎች ..... 15

2.9. የዕቅዱ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ..... 15

2.10. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና ታሳቢ መፍትሄዎች ..... 16

2.10.1. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ..... 16

2.10.2. ታሳቢ መፍትሔዎች ..... 16

2.11. የ2014 ዕቅድ ማስፈፀሚያ በጀት ..... 16

2.12. የቋሚ ኮሚቴው ዋና ዋና ሥራዎች የአፈፃፀም የጊዜ ሰሌዳ ..... 17

2.13. የግቦችና ተግባራት ዝርዝር የድርጊት መርሃ ግብር ..... 18

## መግቢያ

የኢ.ፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሕገ-መንግሥቱ የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነቱን ለመወጣት በደንብ ቁጥር 3/2014 መሠረት ካደራጃቸው ቋሚ ኮሚቴዎች መካከል የሰው ሃብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አንዱ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ቋሚ ኮሚቴው በተሰጠው ኃላፊነትና ተግባር መሠረት ሕግ የማውጣት ተግባር፣ የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች፣ የሕዝብ ውክልና ሥራዎች እና የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራዎችን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችልና ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግባቸውን አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችን ትኩረት ያደረገ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ አዘጋጅቷል፡፡

ዕቅዱ የሰው ሃብትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2013 ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀም እንደ መነሻ በመውሰድ የተዘጋጀ ሲሆን በውስጡ በክፍል አንድ የመነሻ ሁኔታ ግምገማዎች፣ አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች፣ ጥንካሬዎችና እጥረቶች፣ ቁልፍ ችግርና ቁልፍ ተግባር፣ በክፍል ሁለት የዕቅዱን አጠቃላይ ዓላማ፣ በየሥራ ዘርፉ ያሉ ግቦችን እና ዋና ዋና ተግባራት፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው፣ የአፈፃፀም አቅጣጫ፣ የክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ሥርዓትና የጊዜ ሰሌዳን ይዟል፡፡

## ክፍል አንድ

### 1. የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎች

### 1.1. የሰው ሃብትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2013 ዓ.ም አፈፃፀም ግምገማ እንደ መነሻ

#### 1.1.1. አቅም ግንባታ

የሰው ሃብትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተልዕኮውን መሠረት ያደረገና አግባብነቱ ተመዝኖ ከምክር ቤቱና ከባለ ድርሻ አካላት በሚሰጡ አጫጭር ስልጠናዎች፣ አስፈፃሚ ተቋማት ለቋሚ ኮሚቴው ባዘጋጁት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች እንዲሁም የአስፈፃሚ ተቋማት ዕቅድና አፈፃፀም ሪፖርት ግምገማ ወቅት የተገኙ አቅምና ልምድ እንደ አንድ የአቅም ግምባታ ስልጠና ተወስዶ ለቋሚ ኮሚቴው ሥራ አጋዥ የነበረና ለቀጣይ ዓመትም የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት መሆኑ እንደ አንድ የዕቅዱ መነሻ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

#### 1.1.2. ክትትልና ቁጥጥር

የአስፈፃሚ ተቋማትን የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድና የየሩብ ዓመቱ አፈፃፀም ግምገማ ወቅት የተገኙ ግኝቶችን፣ በመስክ ምልከታና በሕግ አወጣጥ ተግባራት አፈፃፀም ወቅት የነበረው መልካም አፈፃፀም እንዲሁም የነበሩ ጉድለቶች እንደ መነሻ ተወስዷል፡፡ ቋሚ ኮሚቴውና ንዑሳን ኮሚቴዎች የሚመሩበትን ዕቅድና ቼክ ሊስት አዘጋጅቶ ወደ ሥራ መግባቱ፣ የሁሉንም አስፈፃሚ መ/ቤቶችን የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ፣ የየሩብ ዓመቱን ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን በመገምገም ግብረ መልስ መስጠቱ፣ የመስክ ምልከታዎችን ማካሄዱና የተገኘውን ልምድ ለሌሎች አባላት ማካፈሉ፣ በወቅቱ ካጋጠመው የኮሮና ወረርሽኝ ጋር ተያይዞ የቋሚ ኮሚቴው አመራሮች እና አባላት በአስቸጋሪ ሁኔታ ሆነው ተግባራትን በጋራ ለመምራት የተደረጉ ጥረቶች ጥሩ መሆናቸውና ለ2014 በጀት ዓመት ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ተግባር መሆኑን እንደ መነሻ ተወስዷል፡፡

#### 1.1.3. ህግ አወጣጥ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ዋና ዋና ስልጣንና ተግባራት ከሆኑት መካከል ህግ ማውጣት አንዱ ነው፡፡ ይህ ሕገ - መንግሥታዊ ተልዕኮ በተለይም አዲስ ህግ ማውጣት፣ ነባር ሕግ ማሻሻል ወይም መሻር፣ የዓለም ዓቀፍ ስምምነቶችን ማጽደቅና ውሳኔ ማስተላለፍ ተግባራት ውስጥ አንዱ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ለቋሚ ኮሚቴው የተመሩ ረቂቅ ህጎች ባይኖሩም ቋሚ ኮሚቴው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተሳትፎው የጎላ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ለፀደቁ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች የወጡላቸው

መሆኑን፣ ተደራሽነታቸውን እና አፈፃፀማቸውን ከመከታተል አንፃር የነበረውን ውስንነት መስተካከል ካለባቸው ጉዳዮች አንዱ ይሆናል፡፡

#### 1.1.4. የመስክ ምልከታ ሥራዎች

በበጀት ዓመቱ ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸውን አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶችና ተጠሪ ተቋማትን በከተማና ከከተማ ውጪ የመስክ ምልከታ ሥራዎች በአካል በመገኘት በርካታ ሥራዎችን አከናውኗል፡፡ በዚህም በየተቋማቱ በጥንካሬ የታዩት ተጠናክሮ እንዲቀጥሉ እንዲሁም በውስንነትና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ላይ በቀጣይ ማስተካከያ እንዲደረግ የመስክ ምልከታ ሥራው እንደ መነሻ ተወስዷል፡፡

## 1.2. የውጫዊ ሁኔታዎች ግምገማ እንደ መነሻ

### 1.2.1. ዕድሎች

- ምክር ቤቱ ተጠናክሮ አስፈፃሚውን መከታተልና መቆጣጠር እንዳለበት መንግሥት ዕኑ እምነት ያለው መሆኑ ለቋሚ ኮሚቴው ሥራ አቅም የሚፈጥር መሆኑ፣
- አብዛኛው ህዝብ ለአገራዊ ለውጡ ድጋፍና መነሳሳት ያለው መሆኑ፣
- በ6ኛው ሃገራዊ ምርጫ ለተመረጡት የምክር ቤት አባላት የ6 ዓመት የሥራ ተሞክሮ ተቀምሮና ተደራጅቶ መቀመጡ አቅም መሆኑ፣
- የ6 ኛው ምክር ቤት አባላት በትምህርት ዝግጅትና በልምድ ስብጥር የተሻለ መሆኑ፣

### 1.2.2. ስጋቶች

- ወቅታዊ ሀገራዊ ሁኔታው ምክንያት በተለያዩ ቦታዎች የሚታዩ የመፈናቀልና የሰው ህይወት መጥፋት ለክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ አመቺ አለመሆኑ፣
- የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በቀላሉ የሚሰራጭ በመሆኑ በሰው ህይወት፣ በኢኮኖሚውና በመንግሥት ሥራ ላይ ተፅዕኖ ማድረስ የሚችል መሆኑ
- አንዳንድ ሚዲያዎች ገንቢና አጋዥ ሚና ከመጫወት ይልቅ አሉታዊ ተፅዕኖ የማሳደር ሁኔታና የምክር ቤቱ የሚዲያ ባለሙያዎች የአቅም ክፍተት መኖር የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድን ተግባራዊ ለማድረግ እንደ ስጋት የሚወሰዱ ናቸው፡፡

**ቁልፍ ችግር**

- የማስፈጸም አቅም እጥረት፣
- ተጠያቂነትን የማረጋገጥ ውስንነት፣
- በምክር ቤቱ አስቻይ የሥራ ሁኔታ አለመኖሩ፣

**ቁልፍ ተግባር**

- የማስፈፀም አቅም ግንባታን ማሳደግ፣
- የቋሚ ኮሚቴዎችን የውሳኔ ሰጪነት አቅም ማሳደግ፣
- በምክር ቤቱ አስቻይ የሥራ ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ፣

## ክፍል ሁለት

### 2. የ2014 ዓ.ም የቋሚ ኮሚቴው ዕቅድ

#### 2.1. የዕቅዱ አጠቃላይ ዓላማ

- በ2014 በጀት ዓመት በአስፈፃሚ መ/ቤቶችና በተጠሪ ተቋማት የተጣሉ ግቦች በትክክል እንዲሳኩ በህግ አወጣጥ፣ ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ በማድረግ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣
- የቋሚ ኮሚቴውን ሁለንተናዊ አቅምን በማሳደግ የክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ሥራን ማጠናከር፣
- በምክር ቤቱ ጽ/ቤት አስቻይ የሥራ ሁኔታ እንዲፈጠር የክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ማድረግ፣

#### 2.2. የዕቅዱ ዝርዝር ዓላማዎች

- የሕግ ክፍት ያሉባቸውን የአስፈፃሚ ተቋማትን ተግባራት በመለየት ሕግ እንዲወጣላቸውና በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማሻሻያ እንዲደረግላቸው ማድረግ፣
- የአስፈፃሚ አካላት ዕቅድ ከሃገራዊ ዕቅድ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ፣
- የአስፈፃሚ አካላት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ከዕቅዳቸው ጋር በማነፃፀር ያላቸውን አፈፃፀም በንፅፅር ግብረ-መልስ መስጠት እና ድጋፍ ማድረግ፣
- የአስፈፃሚ አካላት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ተዓማኒነትን በመስክ ምልከታ ማረጋገጥ፣
- አስፈፃሚ መ/ቤቶችንና በሥራቸው ያሉ ተጠሪ ተቋማትን በፊት ለፊት በመጥራት መገምገምና ግብረ መልስ መስጠት፣
- ከመራጭ ህዝብ በምክር ቤት አባላት የተሰበሰቡ ጥያቄዎችን በምክር ቤቱ በኩል በመቀበል የሚመለከታቸው አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ፣
- ወደ ቋሚ ኮሚቴው የሚቀርቡ ቅሬታዎችና ጥቆማዎችን በመመርመር አፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ፣
- አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት በሕግ በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት መሠረትና በክትልና ቁጥጥር ወቅት በግብረ መልስ የተሰጡ ማስተካከያዎችን ተግባራዊ ባላደረጉ ላይ ተጠያቂነትን ማስፈን፣

- የምክር ቤቱ ጽ/ቤት በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር ተጠያቂነት ባለው መልኩ ክትትልና ድጋፍ ማድግ፣

## 2.3. ለሰው ሃብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ዝርዝር

### I. የትምህርት ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት

1. የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች፣ (45)
2. የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት፣
3. ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ፣
4. ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ፣
5. የትምህርትና ስልጠና ባለሥልጣን

### II. የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት

1. የኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት
2. የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን፣
3. የስፔስ ቴክኖሎጂና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት፣
4. የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን

### III. የሥራና ክህሎት ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት

1. የፌዴራል ቴክኒካል ዩኒቨርሲቲ፣
2. የግብርና ቴክኒክና ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች፣
3. የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት

### IV. የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንና ተጠሪ ተቋማት፤

1. የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ፣
2. የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት

### V. የቤተ-መንግሥት አስተዳደር፣

### VI. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት

## 2.4. የዝግጅት ምዕራፍ ሥራዎች

### ግብ 1፡ የቋሚ ኮሚቴውን ዕቅድ ማዘጋጀትና መከለስ

### ዝርዝር ተግባራት

ተግባር 1፡ የምክር ቤቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ የ2013 በጀት ዓመት የሰው ሃብትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና የሴቶች፣ ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መነሻ በማድረግ የሰው ሃብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድን ማዘጋጀት፣

ተግባር 2፡ የቋሚ ኮሚቴውን የክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ቼክሊስት ማዘጋጀት፣

ተግባር 3፡ በፊት ለፊት መድረክ ሪፖርታቸውን የሚያቀርቡበትን፣ የመስክ ምልከታ ዕቅድና የተቋማት የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት፣

ተግባር 4፡ በተዘጋጀው የቋሚ ኮሚቴው ዕቅድ፣ የክትትልና ቁጥጥር ቼክሊስትና የተቋማት የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ ሰሌዳ ላይ ለቋሚ ኮሚቴው አመራርና አባላት በማቅረብ (ኦሬንቴሽን በመስጠት) የሚሰጡ ግብዓቶችን በማካተት የሥራ መመሪያ አድርጐ መሥራት ይጠበቃል፡፡

**ግብ 2፡ ተሞክሮ ማካፈል፣**

ተግባር 1፡ ለቋሚ ኮሚቴ አመራሮችና አባላት የነበረውን የ6 ዓመት ተሞክሮ እንዲያገኙ ማድረግ፣

ተግባር 2፡ ቋሚ ኮሚቴው ከሌሎች አቻ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ ከክልል ምክር ቤቶች ቋሚ ኮሚቴዎችና አግባነት ካላቸው የውጪ ሀገራት ተቋማት ጋር ልምድና ተሞክሮ ልውውጥ ማድረግ፣

ተግባር 3፡ ቋሚ ኮሚቴው በተግባር አፈፃፀም ወቅት የሚገኙ የተሻሉ ተሞክሮዎችን መቀመርና ለሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች ማካፈል፣

## 2.5. የተግባር ምዕራፍ ሥራዎች

**ግብ 1፡- የአቅም ግንባታ ሥራዎች ማከናወን፣**

**ተግባር 1፡ የቋሚ ኮሚቴ አባላትን አቅም መገንባት፣**

**ዝርዝር ተግባራት፡-**

- የቋሚ ኮሚቴው አባላት አዲስ በመሆናቸው የሥራ ማስተዋወቅ ሥልጠናዎች (Induction Training) በምክር ቤቱ፣ በምክር ቤቱ ፅ/ቤት፣ በአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት በሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ላይ ተሳትፎ ማድረግ፣
- ለቋሚ ኮሚቴው ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት አኳያ በምክር ቤቱና በምክር ቤቱ ጽ/ቤትና በቋሚ ኮሚቴው በሚዘጋጁ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ላይ በመሳተፍ አቅምን ማጎልበት፣

- በሚመለከታቸው አካላት በሚዘጋጁ ስልጠናዎች፣ ሴሚናሮች፣ አውደ ምክክርና ጥናቶች ላይ አባላት እንዲሳተፉ ጥሪ ሲቀርብ እንዲሳተፉና ከስልጠና መልስ ሪፖርት ለኮሚቴው በማቅረብ ያገኙትን ዕውቀት ለተቀሩት አባላት እንዲያካፍሉ ማድረግ፣
- ቋሚ ኮሚቴው ተግባራቶችን በሚከናውንባቸው ሂደቶችን የአባላትን አቅም ሊገነባ በሚያስችል መልኩ መጠቀም፣

## ግብ 2፡- የክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ሥራዎችን ማከናወን፣

**ተግባር 1፡- የአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችንና ተጠሪ ተቋማትን የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ፣ የየሩብ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም እና የማጠቃለያ ሪፖርት መገምገም፣**

### ዝርዝር ተግባራት

- የ2014 በጀት ዓመት የአስፈፃሚ አካላት ዕቅዶችን መገምገም፣ ግብረ መልስ መስጠት እና በግብረ-መልሱ መሰረት መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ማስተካከያ መደረጉን ማረጋገጥ፣
- በአስፈፃሚ ተቋማት የቀረቡ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን መገምገም፣ ግብረ መልስ መስጠትና በተሰጠው ግብረ መልስ መሠረት መፈፀሙን ማረጋጥ፣
- የአስፈፃሚ መ/ቤቶችንና ተጠሪ ተቋማትን ዕቅድ እና ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በፊት ለፊት መድረክ ግምገማ ማድረግና ግብረ መልስ መስጠት፣
- በዋና ኦዲተር የተሰጡ የኦዲት ግኝት አስተያየቶችን መነሻ በማድረግ ተቋማት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ማድረግ፣
- በዋና ኦዲተር ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸውን ተቋማት በተመለከተ የምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔና የየተቋማቱ ኃላፊዎች በተገኙበት ቀርበው ውይይት እንዲደረግበትና መፍትሄ እንዲሰጥበት ማስቻል፣

**ተግባር 2፡- የመስክ ምልከታ ሥራዎችን ማከናወን፣**

### ዝርዝር ተግባራት

- በተመረጡ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችና በሥራቸው ያሉ ተጠሪ ተቋማት እንዲሁም ዩኒቨርስቲዎች ላይ ቼክ- ሊስት በማዘጋጀት የመስክ ምልከታ ማድረግ፣

  በዚሁ መሠረት፤

  - ከከተማ ውጪ አምስት የመስክ ምልከታ ሥራዎችን ማካሄድ፣ ዩኒቨርሲቲዎቹ የተመረጡበት አግባብ በቦታ አቀማመጥ፣ በዩኒቨርሲቲዎቹ ትውልድና በ2013 ዓ.ም በመስክ ምልታ ያልተካተቱትን በመለየት፣
    - ✓ አርሲ ዩኒቨርሲቲ፣ መዳዋላቡ ዩኒቨርሲቲና አጋርፋ ግብርና ኮሌጅ
    - ✓ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ፣ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲና ወላይታ ሶዶ ግብርና ኮሌጅ፣
    - ✓ ሀረማያ፣ ኦዳ ቡልቱምና ቀብሪደሃር ዩኒቨርሲቲ
    - ✓ ጅማ፣ ቦንጋና ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ
    - ✓ ደብረማርቆስ፣ እንጂባራና ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ
    - ✓ ጎንደርና ደባርቅ ዩኒቨርሲቲዎች ይሆናሉ፡፡
  - በከተማ ውስጥ የመስክ መልከታ የሚሸፈኑት
    - ✓ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የሀገር ዓቀፍ ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት፣ የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣንና እና ከግል ከፍተኛ ትምህር ተቋት ሪፍትቫሊና አድማስ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ፣
    - ✓ የፌዴራል ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ቴክኒካል ዩኒቨርሲቲ፣ የቱሪዝም ማሰልጠና ኢንስቲትዩት፣
    - ✓ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣ የአፍሪካ ልህቀት ማዕከል፣ የቤተ-መንግሥት አስተዳደር፣
    - ✓ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ኢንስቲትዩት፣ የኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣
    - ✓ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት ይሆናሉ፡፡

**ተግባር 3፡- ለምክር ቤቱ በአካል ሪፖርት የሚያቀርቡ አስፈፃሚ መ/ቤቶችን መከታተልና ማስፈፀም፣**

**ዝርዝር ተግባራት**

- ለምክር ቤቱ በመደበኛ ጉባዔ ሪፖርታቸውን የሚያቀርቡ፡-
  - ✓ የትምህርት ሚኒስቴር፣
  - ✓ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣

- ✓ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እና
- ✓ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሪፖርታቸውን በመገምገም አስተያየትና ጥያቄዎች በማዘጋጀት በአካል ቀርበው ውይይት ይደረጋል፡፡

**ተግባር 4፡- ለቋሚ ኮሚቴው በአካል ሪፖርት የሚያቀርቡ አስፈፃሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማትን መለየትና ማስፈፀም፣**

- ➢ ለቋሚ ኮሚቴው ዕቅዳቸውንና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርታቸውን በፊት ለፊት መድረክ የሚያቀርቡ፡-
  - ✓ የትምህርት ሚኒስቴርና የተመረጡ ተጠሪ ተቋማት፣
  - ✓ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት፣
  - ✓ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፣
  - ✓ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ፣
  - ✓ ወራቤ ዩኒቨርሲቲ፣
  - ✓ ወለጋ ዩኒቨርሲቲ፣
  - ✓ ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርስቲ፣
  - ✓ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ እና
  - ✓ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንና ተጠሪ ተቋማት በመገምገም አስተያየትና ጥያቄዎችን በማዘጋጀት በአካል ቀርበው ውይይት ይደረጋል፡፡
- ➢ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ዓመታዊ የጋራ የውይይት መድረክ ማካሄድ፣
- ➢ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ ኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን እና ተጠሪ ተቋማት ዓመታዊ የጋራ የውይይት መድረክ ማካሄድ፣

**ተግባር 5፡- ከተለያዩ አካላት የሚቀርቡ አግባብነት ያላቸው ቅሬታዎችና ጥቆማዎችን በማጣራት ወቅታዊ ምላሽ እንዲሰጣቸው ማስቻል**

**ዝርዝር ተግባራት፡-**

- ለሚቀርቡ ቅሬታዎችና ጥቆማዎች በም/ቤቱ የአሠራርና የአባላት ሥነ-ምግባር ደንብ 6/2008 መሠረት መርምሮ የውሳኔ ሃሳብና አስተያየት ማቅረብ፣
- ተመርምሮ የተገኘውን የውሳኔ ሃሳብና አስተያየት ለሚመለከተው አስፈፃሚ መ/ቤት ምላሽ እንዲሰጥበት በደብዳቤ ማሳወቅ፣
- በአስፈፃሚ መ/ቤቱ በኩል የተሰጠውን ምላሽ ለጥቆማና ቅሬታ አቅራቢዎች ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ፣
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመጡ ቅሬታዎች እና ጥቆማዎች ለሚመለከታቸዉ ዴሞክራሲ ተቋማት በመላክ ጥናት አድርገው የውሳኔ ሐሳብ በማዘጋጀት እንዲደግፉ ማድረግ፣

**ተግባር 6፡- ከአፈ-ጉባዔ የሚሰጡ ተግባራትን መከታተልና መፈፀም**

**ዝርዝር ተግባራት**

- ከመራጭ ህዝብ በምክር ቤት አባላት የተሰበሰቡ ጥያቄዎችን በምክር ቤቱ በኩል መቀበል፣
- የቀረቡ ጉዳዮች በሚመለከተው አስፈፃሚ አካል ተፈፃሚነታቸውና ምላሻቸውን መከታተልና ሪፖርቱን ለምክር ቤቱ እንዲልኩ ማድረግ፣
- በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተገቢውን ምላሽ በማይሰጡ አስፈፃሚ አካላት ላይ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣

**ግብ 2፡- ሕግ ማውጣት**

**ተግባር 1፡- በምክር ቤቱ ለቋሚ ኮሚቴው የሚመሩ ረቂቅ አዋጆችን በመመርመርና የውሳኔ ሃሳብ በማዘጋጀት ማቅረብና ማፀደቅ፣**

**ዝርዝር ተግባራት**

- በምክር ቤቱ የተመሩ ረቂቅ አዋጆችን በተመለከተ ከምክር ቤት አባላት በመጀመሪያ ንባብ ወቅት የተነሱ ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን ማደራጀት፣
- በረቂቅ ዓዋጁ ላይ ከቋሚ ኮሚቴ አባላት የሚቀርቡ ጥያቄዎችና አስተያየቶችን ለአስረጂ መድረክ ዝግጁ ማድረግ፣
- የአስረጂዎች መድረክ በማዘጋጀት በረቂቅ ዓዋጁ ላይ ውይይት ማካሄድና ግብዓቶችን ማሰባሰብ፣
- በረቂቅ ዓዋጁ ላይ የሕዝብ ይፋ ውይይት መድረክ በማዘጋጀት ግብዓት መሰብሰብ፣
- ረቂቅ ሕጎቹ በም/ቤቱ ድረ-ገፅ ተጭነው የሚመለከታቸው አካላት አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ማድረግ፣
- በረቂቅ ህጎቹ ላይ የሕግ ባለሙያዎችንና ሌሎች ባለሙያዎችን በማሳተፍ አስተያየት ለኮሚቴው እንዲያቀርቡ ማድረግ፣

- የተሰበሰቡ አስተያየቶችን መሠረት በማድረግ የሚመለከተው አስፈፃሚ አካል አስተያየት እንዲሰጥ ማድረግ፣
- በረቂቅ ዓዋጁ ላይ ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ በተያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ በማቅረብ ማፀደቅ፣
- በክትትልና ቁጥጥር ወቅት የሕግ ክፍተት የሚታዩባቸው ጉዳዮች ላይ ሕግ እንዲወጣላቸው ሃሳብ ማመንጨትና ተቀባይነት ሲያገኝ ረቂቅ ሕግ እንዲዘጋጅ ማድረግ፣

**ተግባር 2፡- በምክር ቤቱ ፀድቀው ለወጡ ዓዋጆች ተገቢ ደንቦችና መመሪያዎች መውጣታቸውን፣ ተደራሽና ተፈፃሚ መሆናቸውን መከታተል፣**

**ዝርዝር ተግባራት**

- በምክር ቤቱ ፀድቀው ለወጡ ዓዋጆች በሦስት ወራት ውስጥ ደንብና መመሪያዎች ወጥተው ተደራሽ መሆናቸውንና ከዋናው ዓዋጅ ጋር መጣጣማቸውን መከታተል፣
- የወጡ ዓዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች እየተሠራባቸው መሆኑን ማረጋገጥና ተግባራዊ በማያደርጉት አካላት ላይ ተጠያቂነትን ማስፈን፣

## ግብ 3፡- የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮች

**ተግባር 1፡- በአስፈፃሚ መ/ቤትና በስራቸው ባሉ ተጠሪ ተቋማት ዕቅድና ሪፖርት የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮች የተካተቱና የተፈፀሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ**

**ዝርዝር ተግባራት**

- የአስፈፃሚ ተቋማት ዕቅድ የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን ያካተቱና በበጀት መደገፋቸውን መፈተሽ፣

- የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን በሁሉም ተቋማት በዕቅዱ መሠረት መፈፀማቸውን መቆጣጠርና መከታተል፣

## ግብ 4፡- የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ መከላከልና መቆጣጠር

**ተግባር 1፡- አስፈፃሚ ተቋማት የኮቪድ-19 ለመከላከልና ለመቆጣጠር በዕቅዳቸውና በሪፖርታቸው መካተቱን ማረጋገጥ**

**ዝርዝር ተግባራት**

- ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸው አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች የኮቪድ-19ን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የታቀዱና የተሠሩ ሥራዎችን መከታተል፣
- ቋሚ ኮሚቴው የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ሥራውን ሲወጣ የኮቪድ-19ን ፕሮቶኮልን ጠብቆ መሥራት፣

**ግብ 5፡ ከሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት ያሉበትን ሁኔታ በመገምገም አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣**

**ዝርዝር ተግባራት**

- ጦርነቱ ባስከተለው ቀውስ ምክንያት አገልግሎታቸው የተስተጓጎሉ የትምህርት ተቋማት ወደ ሥራ የሚገቡበትን ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲመቻች ማድረግ፣
- በጦርነት ምክንያት ትምህርታቸውን ያቋረጡ፣ ከአካባቢያቸው የተፈናቀሉ ተማሪዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ ማድረግ፣
- በተፈጠረው ቀውስ ምክንያት ከሥራ ገበታቸው የተፈናቀሉ መምህራንና ሠራተኞችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መልሶ ማቋቋምና ወደ ሥራ ገበታቸው እንዲመለሱ ማድረግ፣

## ግብ 6፡ በዋና ኦዲተር የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች ማስተካከያ መደረጉን ማረጋገጥ

## ዝርዝር ተግባራት

- አስፈፃሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማትን በማስመልከት በዋና ኦዲተር የተሰጡና ማስተካከያ የሚሹ የኦዲት አስተያየቶችን በመለየት የክትትልና፣ ቁጥጥር አካል ማድረግ፣

- አስፈፃሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት በዋና ኦዲተር የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶችን በተመለከተ የማስተካከያ መርሃ ግብር በማዘጋጀት የዕቅድና የአፈፃፀማቸው አካል እንዲያደርጉ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣

**ግብ 7፡- ድጋፍና ተጠያቂነት**

- አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችና ተጠሪ ተቋማትን ዕቅዳቸውን ለማሳካት የሚያጋጥሟቸውን ዋና ዋና ተግዳሮቶችን በመለየት ድጋፍ ማድረግ፣ ባለ ድርሻ አካላትን በማሳተፍ መፍትሄ መስጠት፣

- መልካም አፈፃፀም ያላቸውን አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችንና ተጠሪ ተቋማትን ለማበረታታት እውቅና መስጠት፣

- በአፈፃፀማቸው ጉድለት ያሳዩ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችንና ተጠሪ ተቋማትን ተጠያቂነትን ለማስፈን፡-
    - የቃልና የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣
    - በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ብልሹ ተግባሩን ለሕዝብ ማጋለጥ፣
    - በአፈ ጉባኤ በኩል ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀርቦ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፣
    - የኦዲት ግኝት፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰትና ከፍተኛ የሥነ-ምግባር ችግር ጋር ተያይዞ እንደ ጉዳዩ ክብደት የተቋሙ የሥራ ኃላፊዎችን በሕግ ተጠያቂ ማድረግ፣

## 2.6. ሙያዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ

## ግብ 1፡- ለቋሚ ኮሚቴው ሙያዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ መስጠት፣

**ዝርዝር ተግባራት**

- ቋሚ ኮሚቴው በሚያደርጋቸው የክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ፣ በሕግ ማውጣትና በሕዝብ ውክልና ተግባራት ሙያዊና አስተዳራዊ ድጋፍ መስጠት፣
- በዓመቱ ለኮሚቴው ሥራዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ለይቶ በወቅቱ እንዲቀርቡ ክትትል ማድረግ፣
- የፊት ለፊት ውይይት መድረክና የመስክ ምልከታ ሥራዎችን በማመቻቸት ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣

- በአስፈፃሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት ዕቅዶችና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ግብረ-መልሶችን ማዘጋጀት፣ ሙያዊ አስተያየት መስጠት፣ በኮሚቴው የሚሰጡ ግብዓቶችን በማካተት ለተቋማቱ ተደራሽ ማድረግ፣
- ከቋሚ ኮሚቴውና አባላቱ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ አጫጭር ሙያዊ ማብራሪያ በማዘጋጀት ማቅረብ፣
- የቋሚ ኮሚቴው ዕቅድና አፈፃፀም ሪፖርት፣ የዕቅድ ማስፈፀሚያ ቼክ ሊስት እና ፕሮግራም በጀት ከቋሚ ኮሚቴው አባላት ጋር በመሆን ማዘጋጀትና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ማድረግ፣
- ለቋሚ ኮሚቴው የሚዘጋጁ የአቅም ግንባታ መድረኮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ማመቻቸት፣

### 2.7. የማጠቃለያ ምዕራፍ ሥራዎች

**ግብ 1፡ የቋሚ ኮሚቴውን የማጠቃለያ ሥራዎች ማከናወን**

ተግባር 1፡ ቋሚ ኮሚቴ የሚከታተላቸውን አስፈፃሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማትን የበጀት ዓመቱን የማጠቃለያ ምዕራፍ ተግባራት ማከናወናቸውን ማረጋገጥ፣

**ዝርዝር ተግባራት**

- በዕቅድ የተቀመጡ ግቦች መሳካታቸውና አለመሳካታቸውን መለየትና መረጃ አደራጅቶ መያዝ፣
- የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን ተቋማት በተዘጋጀው መሥፈርት መሠረት ደረጃና እውቅና መስጠት፣

ተግባር 2፡ የቋሚ ኮሚቴውን የ2014 በጀት ዓመት ሥራ ማጠቃለል

- የቋሚ ኮሚቴውን የ2014 በጀት ዓመት ማጠቃለያ ሪፖርት በማዘጋጀት መገምገምና ለሚመለከተው አካል መላክ፣
- ቋሚ ኮሚቴው በበጀት ዓመቱ በአፈፃፀም ወቅት የነበሩ ጥንካሬዎችና እጥረቶችን በመለየት መልካም ተሞክሮዎችን መቀመርና ልምድ መውሰድ፣
- የቋሚ ኮሚቴውን የ2015 በጀት ዓመት መነሻ ዕቅድ ማዘጋጀት፣

### 2.8. አጠቃላይ የዕቅዱ አፈፃፀም አቅጣጫዎች

- የጋራ ስኬትን መነሻ በማድረግ በሁሉም ተግባራት ቅንጅታዊ አሠራርን እና የመናበብ አካሄድን የተከተለ አፈፃፀም ማረጋገጥ፤
- በሁሉም ተግባራት የአሳታፊነት፣ የግልፅነት እና የተጠያቂነት አሠራርን ማስፈን፤
- ወጪና ጊዜ ቆጣቢ አሠራሮችን ተግባራዊ ማድረግ፣
- በእያንዳንዱ ተግባራት የዜጎችን ተጠቃሚነት የማረጋገጥ አቅጣጫን መከተል፣
- የተቋማት ግንባታን መሠረት ያደረገ አቅጣጫን መከተል፣

### 2.9. የዕቅዱ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት

- ቋሚ ኮሚቴው በየሳምንቱ አንድ ቀን የተሠሩ ሥራዎች ላይ ውይይት ያደርጋል፣
- ኮሚቴው በየወሩ አጭር ወርሃዊ አፈፃፀም ግምገማ ያካሄዳል፣ የቀጣይ ወር ተግባራት ላይ መግባባትና የሥራ ፕሮግራም ይዘጋጃል፣

- ኮሚቴው የየወሩን፣ የ6 ወር እና ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በማዘጋጀትና የጋራ በማድረግ ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ፣

## 2.10. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና ታሳቢ መፍትሄዎች

### 2.10.1. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች

- ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸው ተቋማት መብዛትና መስፋት ከቋሚ ኮሚቴው ቁጥር ማነስ አንፃር በክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ተግባር ላይ ጫና የሚፈጥር መሆኑ፣
- የቋሚ ኮሚቴውን ተልዕኮና ተግባራትን በስኬት ለመፈፀም በምክር ቤቱ ጽ/ቤት በኩል የአሠራር ሥርዓት፣ የማስፈፀም አቅም ክፍተትና የመደገፍ ዝግጁነት ማነስ፣
- ኮቪድ-19 በቋሚ ኮሚቴው ሥራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥር የሚችል መሆኑ፣
- በሀገራዊ ቀውሱ ምክንያት በቋሚ ኮሚቴው የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑ፣
- የአስፈፃሚ መ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች በወቅታዊ ሀገራዊ ተልዕኮዎች ምክንያት መደበኛ ሥራቸውን መምራትና በወቅቱ ሪፖርት ማድረግ ላይ ጫና የሚፈጥር መሆኑ፣

### 2.10.2. ታሳቢ መፍትሔዎች

- ለክትትል ቁጥጥርና ድጋፍ ተግባር ያለውን የሰው ሃይል ሙሉ ጊዜውን ተጠቅሞ ተግባራትን እንዲያከናውን ማስቻል፣
- በምክር ቤቱ ጽ/ቤት የሚታዩትን የአሠራር ክፍተቶች በተመለከተ በክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ መፍትሄ እንዲገኝ ማድረግ፣
- ኮቪድ-19 ለመከላከል የወጣውን ፕሮቶኮል ተግባራዊ ማድረግ፣
- በሀገራዊ ተጽዕኖ ውስጥ በመሆን ተልዕኮዎችን በብቃት ለመፈፀም ጥረት ማድረግ፣
- በሀገራዊ ቀውስ ምክንያት የተቋማት የሥራ ኃላፊዎች በመደበኛ ሥራቸው መገኘት በማይችሉበት ጊዜ ለሚወክሉት አካል ጥብቅ የሆነ ስምሪት እንዲሰጡ ማድረግ፣

## 2.11. የ2014 ዕቅድ ማስፈፀሚያ በጀት

- የሰው ሀብት ልማትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች  ዳዮች ቋሚ ኮሚቴ 2014 በጀት ዓመት ፍላጎት  ጠቅላላ ድምር 2,826,947.00/ሁለት ሚሊየን ስምንት መቶ ሃያ ስድስት

ሺ. ዘጠኝ መቶ አርባ ሰባት ብር/ ሲሆን የበጀት ዝርዝሩ በፕሮግራም በጀት ላይ ላይ ተሠርቶ አባሪ ተደርጓል፡፡

## 2.12. የቋሚ ኮሚቴው ዋና ዋና ሥራዎች የአፈፃፀም የጊዜ ሰሌዳ

- የቋሚ ኮሚቴውን የዕቅድ ማስፈፀሚያ ቼክሊስት ማዘጋጀት ከህዳር 07—15/2014 ዓ/ም፣
- ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸውን የአስፈፃሚ መ/ቤቶችና የተጠሪ ተቋማትን የተከለሰ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ እና የ1ኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ከህዳር 01—10/2014 ዓ/ም ይልካሉ፣
- ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸውን የአስፈፃሚ መ/ቤቶችና የተጠሪ ተቋማትን የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ እና የ1ኛ ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ማድረግና ግብረ መልስ መስጠት፣ ከህዳር 11 — 30/2014 ዓ/ም
- ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸው የአስፈፃሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማትን የ6 ወር የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መላክ፣ ከጥር 01 — 05/2014 ዓ/ም
- ኮሚቴው የሚከታተላቸውን የአስፈፃሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማትን የ6 ወር የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ማድረግና ግብረ መልስ መስጠት፣ ከጥር 06 — 20/2014 ዓ/ም
- ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸው የአስፈፃሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማትን የ9 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት መላክ፣ ከሚያዝያ 01 — 05/2014 ዓ/ም
- ኮሚቴው የሚከታተላቸውን የአስፈፃሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማትን የ9 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ማድረግና ግብረ መልስ መስጠት፣ ከሚያዝያ 06 — 30/2014 ዓ/ም
- የከተማ መስክ ምልከታና ከከተማ ውጪ የሚካሄዱ መስክ ምልከታዎች ከታህሳስ 05—ግንቦት 30/2014 ዓ/ም
- ኮሚቴው የሚከታተላቸውን የአስፈፃሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማትን በፊት ለፊት መድረክ ውይይት ማድረግና ግብረ መልስ መስጠት፣ ከታህሳስ 05—ሰኔ 10/2014 ዓ/ም
- የቋሚ ኮሚቴው የ2014 በጀት ዓመት የሥራ አፈፃፀም ማጠቃለያ ሪፖርት ማዘጋጀት መገምገምና መላክ፣ ከሰኔ 15—30/2014 ዓ/ም
- የ2015 በጀት ዓመት መነሻ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ ከሰኔ 15—30/2014 ዓ/ም

## 2.13. የግቦችና ተግባራት ዝርዝር የድርጊት መርሃ ግብር

| ተ.ቁ | የታቀዱ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት | ተግባሩ የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | | | | | | | | | ፈፃሚ አካል | ምር መራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | | | 2ኛ ሩብ ዓመት | | | 3ኛ ሩብ ዓመት | | | 4ኛ ሩብ ዓመት | | | | |
| | | ሐምሌ | ነሐሴ | መስከረ | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዝያ | ግንቦት | ሰኔ | | |
| 1 | የዝግጅት ምዕራፍ ሥራዎች | | | | | | | | | | | | | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | ግብ 1፡ የቋሚ ኮሚቴውን ዕቅድ፣ ቼክ ሊስት ማዘጋጀት | | | | | | | | | | | | | | |
| | ➢ የምክር ቤቱን መሪ ዕቅድ መነሻ በማድረግ የቋሚ ኮሚቴውን የ2014 ዕቅድ ማዘጋጀት፣ | | | | | ✓ | | | | | | | | >> | |
| | ➢ የቋሚ ኮሚቴው የክትትልና ድጋፍ ቼክ-ሊስት በማዘጋጀትና የጋራ በማድረግ ወደ ሥራ ማስገባት፣ | | | | | ✓ | | | | | | | | >> | |
| | ➢ የመስክ ምልከታ ዕቅድና የተቋማት የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት፣ | | | | | ✓ | | | | | | | | >> | |
| | ➢ በተዘጋጀው ዕቅድ፣ የክትትልና ቁጥጥር ቼክ-ሊስትና የተቋማት የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ ሰሌዳ ላይ ለቋሚ ኮሚቴው አመራርና አባላት በማቅረብ (ኦሬንቴሽን በመስጠት) የሚቀርቡ ማስተካከያዎችን በመቀበል የተከለሰውን ዕቅድ በማዳበር ለሚመለከተው አካል መላክ፣ | | | | | ✓ | | | | | | | | >> | |
| | **ግብ 2፡ ተሞክሮ ማካፈል፣** | | | | | | | | | | | | | | |
| | ➢ ለቋሚ ኮሚቴ አመራሮችና አባላት የነበረውን የ6 ዓመት ተሞክሮ እንዲያገኙ ማድረግ፣ | | | | | ✓ | | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ➢ ቋሚ ኮሚቴው ከሌሎች አቻ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ ከክልል ምክር ቤቶች ቋሚ ኮሚቴዎችና አግባነት ካላቸው የውጪ ሀገራት ተቋማት ጋር ልምድና ተሞክሮ ልውውጥ ማድረግ፣ | | | | | | | | | ✓ | | | | |
| | ➢ ቋሚ ኮሚቴው በተግባር አፈፃፀም ወቅት የሚገኙ የተሻሉ ተሞክሮዎችን መቀመርና ለሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች ማካፈል፣ | | | | | | | | | | | ✓ | | |
| 2 | **የተግባር ምዕራፍ ሥራዎች** | | | | | | | | | | | | | |
| | **ግብ 1፡- የአቅም ግንባታ ሥራዎች ተከናውነዋል** | | | | | | | | | | | | | |
| | ➢ የቋሚ ኮሚቴው አባላት አዲስ በመሆናቸው የሥራ ማስተዋወቅ ሥልጠናዎች (Induction Training) በምክር ቤቱ፣ በምክር ቤቱ ፅ/ቤት፣ በአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት በሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ላይ ተሳትፎ ማድረግ፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | | | | | | በምክር ቤቱ፣ በምክር ቤቱ ጽ/ቤት | |
| | ➢ ለቋሚ ኮሚቴው ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት አኳያ በምክር ቤቱና በምክር ቤቱ ጽ/ቤትና በቋሚ ኮሚቴው በሚዘጋጁ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ላይ በመሳተፍ አቅምን ማጎልበት፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | በምክር ቤቱ ጽ/ቤት፣ በቋሚ ኮሚቴው | |
| | ➢ በሚመለከታቸው አካላት በሚዘጋጁ ስልጠናዎች፣ ሴሚናሮች፣ አውደ ምክክርና ጥናቶች ላይ አባላት እንዲሳተፉ ጥሪ ሲቀርብ እንዲሳተፉና ከስልጠና መልስ ሪፖርት ለኮሚቴው በማቅረብ ያገኙትን ዕውቀት ለተቀሩት አባላት እንዲያካፍሉ ማድረግ፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | በቋሚ ኮሚቴው አባላት | |
| | ➢ ቋሚ ኮሚቴው ተግባራቶችን በሚከናውንባቸው ሂደቶችን የአባላትን አቅም ሊገነባ በሚያስችል መልኩ መጠቀም፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | በቋሚ ኮሚቴው አባላት | |
| 3 | **የአበይት ግቦችና ዝርዝር ተግባራት** | | | | | | | | | | | | | |
| | **ግብ 1፡- የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች ተከናውኗል፣**<br>ተግባር 1፡- የአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችንና ተጠሪ ተቋማትን የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ፣ የየሩብ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም እና የማጠቃለያ ሪፖርት መገምገም፣ | | | | | | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ➢ የ2014 በጀት ዓመት የአስፈፃሚ አካላት ዕቅዶችን መገምገም፣ ግብረ መልስ መስጠት እና በግብረ-መልሱ መሰረት መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ማስተካከያ መደረጉን ማረጋገጥ፣ | | | | | ✓ | ✓ | | | ✓ | | | | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | ➢ በአስፈፃሚ ተቋማት የቀረቡ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን መገምገም፣ ግብረ መልስ መስጠትና በተሰጠው ግብረ መልስ መሠረት መፈፀሙን ማረጋጥ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | ➢ የአስፈፃሚ መ/ቤቶችንና ተጠሪ ተቋማትን ዕቅድ እና ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በፊት ለፊት መድረክ ግምገማ ማድረግና ግብረ መልስ መስጠት፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | ➢ በዋና ኦዲተር የተሰጡ የኦዲት ግኝት አስተያየቶችን መነሻ በማድረግ ተቋማት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ማድረግ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | ➢ በዋና ኦዲተር ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸውን ተቋማት በተመለከተ የምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔና የየተቋማቱ ኃላፊዎች በተገኙበት ቀርበው ውይይት እንዲደረግበትና መፍትሄ እንዲሰጥበት ማስቻል፣ | | | | | | | | | | | ✓ | | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | ተግባር 2፡- የመስክ ምልከታ ሥራዎችን ማከናወን፣ | | | | | | | | | | | | | | |
| | ➢ ቋሚ ኮሚቴው በ2014 በጀት ዓመት በተመረጠ አግባብ ከከተማ ውጭ ስድስት የመስክ ምልከታ ሥራዎችን ማካሄድ፣ | | | | | | | | | | | | | | |
| | ✓ አርሲ፣ መዳዋላቡ ዩኒቨርሲቲና አጋርፋ ግብርና ኮሌጅ | | | | | | ✓ | | | | | | | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | ✓ አርባ ምንጭ፣ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲና ወላይታ ሶዶ ግብርና ኮሌጅ | | | | | | ✓ | | | | | | | >> | |
| | ✓ ሀረማያ፣ ኦዳ ቡልቱምና ቀብሪደሃር ዩኒቨርሲቲ | | | | | | | ✓ | | | | | | >> | |
| | ✓ ጅማና ቦንጋ ዩኒቨርስቲዎች | | | | | | | | | ✓ | | | | >> | |
| | ✓ ደብረማርቆስ፣ እንጂባራና ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ | | | | | | | | | ✓ | | | | >> | |
| | ✓ አምቦ፣ ወልቂጤና ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲዎች | | | | | | | | | | ✓ | | | >> | |

| | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ✓ ጎንደርና ደባርቅ ዩኒቨርሲቲዎች | | | | | | | | | | | ✓ | | | |
| | ➢ **ቋሚ ኮሚቴው በ2014 በጀት ዓመት በተመረጠ አግባብ የከተማ ውስጥ** መስክ ምልከታ ማካሄድ፣ | | | | | | | | | | | | | >> | |
| | ✓ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የሀገር ዓቀፍ ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት፣<br>✓ የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን እና(ሬፍቲቫሊ ዩኒቨርሲቲ፣ አድማስ ዩኒቨርሲቲ) የመስክ ምልከታ ማካሄድ፣ | | | | | | ✓ | | | | | | | >> | |
| | ✓ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመስክ ምልከታ ማካሄድ፣ | | | | | | | | | ✓ | | | | >> | |
| | ✓ የፌዴራል ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ቴክኒካል ዩኒቨርሲቲ የመስክ ምልከታ ማካሄድ፣ | | | | | | | | | | ✓ | | | >> | |
| | ✓ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ኢንስቲትዩት፣ የኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የመስክ ምልከታ ማካሄድ፣ | | | | | | | ✓ | | | | | | >> | |
| | ✓ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣ የቤት-መንግሥት አስተዳደር፣ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ እና የአፍሪካ ልህቀት ማዕከል | | | | | | | | | | ✓ | | | >> | |
| | ተግባር 3፡- ለምክር ቤቱ በአካል ሪፖርት የሚያቀርቡ አስፈፃሚ መ/ቤቶችን መከታተልና ማስፈፀም፣ | | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ ለምክር ቤቱ በመደበኛ ጉባዔ ሪፖርታቸውን የሚያቀርቡ፡-<br>• የትምህርት ሚኒስቴር፣ | | | | | | | ✓ | | | | | | በምክር ቤቱ | |
| | • የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና | | | | | | | ✓ | | | | | | በምክር ቤቱ | |
| | • የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር | | | | | | | | | ✓ | | | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | • ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሪፖርታቸውን በመገምገም አስተያየትናጥያቄዎች በማዘጋጀት በአካል ቀርበው ውይይት ይደረጋል፡፡ | | | | | | | | | ✓ | | | | በምክር ቤቱ | |
| | ተግባር 4፡- ለቋሚ ኮሚቴው በአካል ሪፖርት የሚያቀርቡ አስፈፃሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማትን መለየትና ማስፈፀም፣ | | | | | | | ✓ | | | | | | | |
| | ➢ ለቋሚ ኮሚቴው ዕቅዳቸውንና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርታቸውን በፊት ለፊት መድረክ የሚያቀርቡ፡-<br>• የትምህርት ሚኒስቴርና የተመረጡ ተጠሪ ተቋማት፣ | | | | | | ✓ | | | | | | | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | • ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት፣ | | | | | | | | | ✓ | | | | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | • አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፣ | | | | | | ✓ | | | | | | | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | • ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ፣ | | | | | | | ✓ | | | | | | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | • ወራቤ ዩኒቨርሲቲ፣ | | | | | | | | | ✓ | | | | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | • ወለጋ ዩኒቨርሲቲ፣ | | | | | | | | | | | ✓ | | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | • ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርስቲ እና | | | | | | | | | | | ✓ | | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | • የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | | | | | | | ✓ | | | | | | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | • ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ | | | | | | | | | ✓ | | | | | |
| | ተግባር 5፡- ከተለያዩ አካላት የሚቀርቡ አግባብነት ያላቸው ቅሬታዎችና ጥቆማዎችን በማጣራት ወቅታዊ ምላሽ እንዲሰጣቸው ማስቻል፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | በቋሚ ኮሚቴው | |

| | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ➢ ለሚቀርቡ ቅሬታዎችና ጥቆማዎች በም/ቤቱ የአሠራርና የአባላት ሥነ-ምግባር ደንብ 6/2008 መሠረት መርምሮ የውሳኔ ሃሳብና አስተያየት ማቅረብ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | ➢ ተመርምሮ የተገኘውን የውሳኔ ሃሳብና አስተያየት ለሚመለከተው አስፈፃሚ መ/ቤት ምላሽ እንዲሰጥበት በደብዳቤ ማሳወቅ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | ➢ በአስፈፃሚ መ/ቤቱ በኩል የተሰጠውን ምላሽ ለጥቆማና ቅሬታ አቅራቢዎች ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | ➢ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመጡ ቅሬታዎች እና ጥቆማዎች ለሚመለከታቸዉ ዴሞክራሲ ተቋማት በመላክ ጥናት አድርገው የውሳኔ ሐሳብ በማዘጋጀት እንዲደገፉ ማድረግ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | በቋሚ ኮሚቴው | |
| | ተግባር 6፡- ከአፈ-ጉባዔ የሚሰጡ ተግባራትን መከታተልና መፈጸም | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ ከመራጭ ህዝብ በምክር ቤት አባላት የተሰበሰቡ ጥያቄዎችን በምክር ቤቱ በኩል መቀበል፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ የቀረቡ ጉዳዮች በሚመለከተው አስፈፃሚ አካል ተፈፃሚነታቸውና ምላሻቸውን መከታተልና ሪፖርቱን ለምክር ቤቱ እንዲልኩ ማድረግ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተገቢውን ምላሽ በማይሰጡ አስፈፃሚ አካላት ላይ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | **ግብ 2፡- የሕግ ማውጣት** | | | | | | | | | | | | | | |
| | ተግባር 1፡- በምክር ቤቱ ለቋሚ ኮሚቴው የሚመሩ ረቂቅ አዋጆችን በመመርመርና የውሳኔ ሃሳብ በማዘጋጀት ማቅረብና ማፀደቅ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ በምክር ቤቱ የተመሩ ረቂቅ አዋጆችን በተመለከተ ከምክር ቤት አባላት በመጀመሪያ ንባብ ወቅት የተነሱ ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን ማደራጀት፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ በረቂቅ ዓዋጁ ላይ ከቋሚ ኮሚቴ አባላት የሚቀርቡ ጥያቄዎችና አስተያየቶችን ለአስረጂ መድረክ ዝግጁ ማድረግ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ➢ የአስረጂዎች መድረክ በማዘጋጀት በረቂቅ ዓዋጁ ላይ ውይይት ማካሄድና ግብዓቶችን ማሰባሰብ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ በረቂቅ ዓዋጁ ላይ የሕዝብ ይፋ ውይይት መድረክ በማዘጋጀት ግብዓት መሰብሰብ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ ረቂቅ ሕጎቹ በም/ቤቱ ድረ-ገፅ ተጭነው የሚመለከታቸው አካላት አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ማድረግ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ በረቂቅ ህጎቹ ላይ የሕግ ባለሙያዎችንና ሌሎች ባለሙያዎችን በማሳተፍ አስተያየት ለኮሚቴው እንዲያቀርቡ ማድረግ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ የተሰበሰቡ አስተያየቶችን መሠረት በማድረግ የሚመለከተው አስፈፃሚ አካል አስተያየት እንዲሰጥ ማድረግ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ በረቂቅ ዓዋጁ ላይ ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ በተያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ በማቅረብ ማፀደቅ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ በክትትልና ቁጥጥር ወቅት የሕግ ክፍተት የሚታዩባቸው ጉዳዮች ላይ ሕግ እንዲወጣላቸው ሃሳብ ማመንጨትና ተቀባይነት ሲያገኝ ረቂቅ ሕግ እንዲዘጋጅ ማድረግ፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ተግባር 2፡- በምክር ቤቱ ፀድቀው ለወጡ ዓዋጆች ተገቢ ደንቦችና መመሪያዎች መውጣታቸውን፣ ተደራሽና ተፈፃሚ መሆናቸውን መከታተል፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ በምክር ቤቱ ፀድቀው ለወጡ ዓዋጆች በሦስት ወራት ውስጥ ደንብና መመሪያዎች ወጥተው ተደራሽ መሆናቸውንና ከዋናው ዓዋጅ ጋር መጣጣማቸውን መከታተል፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ የወጡ ዓዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች እየተሠራባቸው መሆኑን ማረጋገጥና ተግባራዊ በማያደርጉት አካላት ላይ ተጠያቂነትን ማስፈን፣ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | **ግብ 3፡- የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮች** | | | | | | | | | | | | | | |
| | ተግባር 1፡- በአስፈፃሚ መ/ቤትና በስራቸው ባሉ ተጠሪ ተቋማት ዕቅድና ሪፖርት የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮች የተካተቱና የተፈፀሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ የአስፈፃሚ ተቋማት ዕቅድ የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን ያካተቱና በበጀት መደገፋቸውን መፈተሽ፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን በሁሉም ተቋማት በዕቅዱ መሠረት መፈፀማቸውን መቆጣጠርና መከታተል፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | **ግብ 4፡- የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን መከላከልና መቆጣጠር** | | | | | | | | | | | | | | |
| | ተግባር 1፡- አስፈፃሚ ተቋማት የኮሮና ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በዕቅዳቸውና በሪፖርታቸው መካተቱን ማረጋገጥ፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸው አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች የኮቪድ-19ን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የታቀዱና የተሠሩ ሥራዎችን መከታተል፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ ቋሚ ኮሚቴው የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ሥራውን ሲወጣ የኮቪድ-19ን ፕሮቶኮልን ጠብቆ መሥራት፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ግብ 5፡ ከሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችና | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ተጠሪ ተቋማት ያሉበትን ሁኔታ በመገምገም አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣ | | | | | | | | | | | | | | |
| | ➢ ጦርነቱ ባስከተለው ቀውስ ምክንያት አገልግሎታቸው የተስተጓጎሉ የትምህርት ተቋማት ወደ ሥራ የሚገቡበትን ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲመቻች ማድረግ፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ በጦርነት ምክንያት ትምህርታቸውን ያቋረጡ፣ ከአካባቢያቸው የተፈናቀሉ ተማሪዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ ማድረግ፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ በተፈጠረው ቀውስ ምክንያት ከሥራ ገበታቸው የተፈናቀሉ መምህራንና ሠራተኞችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መልሶ ማቋቋምና ወደ ሥራ ገበታቸው እንዲመለሱ ማድረግ፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ግብ 6፡ በዋና ኦዲተር የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች ማስተካከያ መደረጉን ማረጋገጥ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ አስፈፃሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማትን በማስመልከት በዋና ኦዲተር የተሰጡና ማስተካከያ የሚሹ የኦዲት አስተያየቶችን በመለየት የክትትልና፣ ቁጥጥር አካል ማድረግ፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ አስፈፃሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት በዋና ኦዲተር የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶችን በተመለከተ የማስተካከያ መርሃ ግብር በማዘጋጀት የዕቅድና የአፈፃፀማቸው አካል እንዲያደርጉ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | **ግብ 7፡- ድጋፍና ተጠያቂነት** | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችና ተጠሪ ተቋማትን ዕቅዳቸውን ለማሳካት የሚያጋጥሟቸውን ዋና ዋና ተግዳሮቶችን በመለየት ድጋፍ ማድረግ፣ ባለ ድርሻ አካላትን በማሳተፍ መፍትሄ መስጠት፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ➢ መልካም አፈፃፀም ያላቸውን አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችንና ተጠሪ ተቋማትን ለማበረታታት እውቅና መስጠት፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ በአፈፃፀማቸው ጉድለት ያሳዩ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችንና ተጠሪ ተቋማትን ተጠያቂነትን ለማስፈን፡-<br>• የቃልና የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣<br>• በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ብልሹ ተግባሩን ለሕዝብ ማጋለጥ (Naming and Shaming) ፣<br>• በአፈ ጉባኤ በኩል ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀርቦ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፣<br>• የኦዲት ግኝት፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰትና ከፍተኛ የሥነ-ምግባር ችግር ጋር ተያይዞ እንደ ጉዳዩ ክብደት የተቋሙ የሥራ ኃላፊዎችን በሕግ ተጠያቂ ማድረግ፣ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | **ሙያዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ**<br><br>**ግብ 1፡- ለቋሚ ኮሚቴው ሙያዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ መስጠት፣**<br>**ዝርዝር ተግባራት** | | | | | | | | | | | | | | |
| | ➢ ቋሚ ኮሚቴው በሚያደርጋቸው የክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ፣ በሕግ ማውጣትና በሕዝብ ውክልና ተግባራት ሙያዊና አስተዳራዊ ድጋፍ መስጠት፣ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ በዓመቱ ለኮሚቴው ሥራዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ለይቶ በወቅቱ እንዲቀርቡ ክትትል ማድረግ፣ | ✓ | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ የፊት ለፊት ውይይት መድረክና የመስክ ምልከታ ሥራዎችን በማመቻቸት ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣ | ✓ | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ➢ በአስፈፃሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት ዕቅዶችና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ግብረ-መልሶችን ማዘጋጀት፣ ሙያዊ አስተያየት መስጠት፣ በኮሚቴው የሚሰጡ ግብዓቶችን በማካተት ለተቋማቱ ተደራሽ ማድረግ፣ | ✓ | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ ከቋሚ ኮሚቴውና አባላቱ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ አጫጭር ሙያዊ ማብራሪያ በማዘጋጀት ማቅረብ፣ | ✓ | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ የቋሚ ኮሚቴው ዕቅድና አፈፃፀም ሪፖርት፣ የዕቅድ ማስፈፀሚያ ቼክ ሊስት እና ፕሮግራም በጀት ከቋሚ ኮሚቴው አባላት ጋር በመሆን ማዘጋጀትና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ማድረግ፣ | ✓ | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | ለቋሚ ኮሚቴው የሚዘጋጁ የአቅም ግንባታ መድረኮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ማመቻቸት፣ | ✓ | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | |
| | **የማጠቃለያ ምዕራፍ ሥራዎች**<br>ግብ 1፡ የቋሚ ኮሚቴውን የማጠቃለያ ሥራዎች ማከናወን | | | | | | | | | | | | | | |
| | ተግባር 1፡ ቋሚ ኮሚቴ የሚከታተላቸውን አስፈፃሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማትን የበጀት ዓመቱን የማጠቃለያ ምዕራፍ ተግባራት ማከናወናቸውን ማረጋገጥ፣ | | | | | | | | | | | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ በዕቅድ የተቀመጡ ግቦች መሳካታቸውና አለመሳካታቸውን መለየትና መረጃ አደራጅቶ መያዝ፣ | | | | | | | | | | | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን ተቋማት በተዘጋጀው መሥፈርት መሠረት ደረጃና እውቅና መስጠት፣ | | | | | | | | | | | ✓ | ✓ | | |
| | **ተግባር 2፡ የቋሚ ኮሚቴውን የ2014 በጀት ዓመት ስራ ማጠቃለል** | | | | | | | | | | | ✓ | ✓ | | |
| | ➢ የቋሚ ኮሚቴውን የ2014 በጀት ዓመት ማጠቃለያ ሪፖርት | | | | | | | | | | | ✓ | ✓ | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በማዘጋጀት መገምገምና ለሚመለከተው አካል መላክ፣ | | | | | | | | | | | | | | |
| | ➢ ቋሚ ኮሚቴው በበጀት ዓመቱ በአፈፃፀም ወቅት የነበሩ ጥንካሬዎችና እጥረቶችን በመለየት መልካም ተሞክሮዎችን መቀመርና ልምድ መውሰድ፣ | | | | | | | | | | | | ✓ | | |
| | ➢ የቋሚ ኮሚቴውን የ2015 በጀት ዓመት መነሻ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ | | | | | | | | | | | | ✓ | | |
| | **የ2014 ዕቅድ ማስፈፀሚያ በጀት**<br>➢ የሰው ሀብት ልማትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ዳዮች ቋሚ ኮሚቴ 2014 በጀት ዓመት ፍላጎት ጠቅላላ ድምር2,826,947.00/ ሁለት ሚሊየን ስምንት መቶ ሃያ ስድስት ሺ ዘጠኝ መቶ አርባ ሰባት ብር/ ሲሆን የበጀት ዝርዝሩ በፕሮግራም በጀት ላይ ላይ ተሠርቶ አባሪ ተደርጓል፡፡ | | | | | | | | | | | | | | |